## ካህን « ጸልዩ በእንተ ጽንዓ ዛቲ » ይበል( ያንብብ)

LITANY PRAYER (The people shall respond after each clause: Egzio Tesehalene)

ይካ. ስለዚች ቦታ መድናት በቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳሞች በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ሽማግሎች በጠቅላላም ስለዚህ ዓለም መጠበቅ ጸልዩ፤ ጌታ ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. በዚች ቦታና በሌሎች ቦታዎች ስለሚገኙ በነፍስ በሥጋ ስለ ታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለኛም ለነርሱም ሕይወቱን ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግ ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. በባሕር በየብስ በወንዝ በቀላይ በሌላውም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም በደስታ ወደ መኖሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ ስለ ዛፎችና ስለ ወይኖች በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዕንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ አብዝቶ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጸሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. አምላካችን ክርስቶስ በገዦችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን ልቡናቸውንም ሁልጊዜ በቸርነቱ እንዲያራ ራልን ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነርሱም የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳት ና አባቶቻችን ጳጳሳት አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ቆሞሳት አባቶቻችን ቀሳውስት ወንድሞቻችን ዲያቆናት አባቶቻችን መነኮሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን ሌሎችም ከክርስ ቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸው። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

www.ethiopianorthodox.org

ይካ. የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖቻችን ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይ ማኖት ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲ ያን ሰላም ጸልዩ። ስለ ሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለ ቦታው ሁሉ መጠበቅ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ሊቀ ጳጳሳቱ አባታችን አቡነ _________ና ብፁዕ አባታችን አቡነ ____ በሕይወት በሞት በኑሮም ስለሚደርስባቸው ሁሉ ጸልዩ። ሕይወታቸውን ጠብቆ ለብዙ ዘመን በመንበረ ስብከታቸው ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

www.ethiopianorthodox.org

ይካ. ምዕመናንን በየስፍራቸው ሁሉ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ ዋጋቸውን እንዲሰጣቸውና ይቅርታን እንዲያደርግላቸው ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ለቊርባን የሚሆን ስንዴውን ዕጣኑን ዘቢቡን የሚነበብባቸው መጻሕፍትን ሌላውንም የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በመስጠት ስለሚያስቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ስማቸውን በያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስላዘዙን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ስለ ታላላቆች አባቶች ጸልዩ። ጌታ በረከትን ሰጥቶ በባለስልጣኖችና በሹማምት ፊት በፈራጆችም አደባባይ ፍቅርን መወደድን ያድላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. በደዌ ሥጋ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ ለባልቴቲቱም አባት እናት ለሌላቸው ለድኆቹ ልጆችና ለተጨነቁት ሰዎች ዘር ለዘሩ እርሻ ላረሱ ለሚሸጡ ለሚገዙ ለተጨነቀችም ሰውነት በማናቸውም ቦታ ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ራርቶ ይቅር እንዲላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. በግዞት በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ አገር ለቀው ለተሰደዱ በአጋንንት አሽክላም ለተያዙ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ከግዞት ከምርኮኝነት ያወጣቸው ዘንድ፤ ይቅርታውንም ሰጥቶ እነርሱንም እኛንም ያድነን ዘንድ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ለነፍሳቸው ይቅርታን እየፈለጉ ክቡር በሆነ በዚህ ስፍራ ስለተሰበሰቡት ሁሉ ጸልዩ። የአምላካችን የጌታችን ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. በዚህ ዓመት ስለዝናም መዝነም ስለ ባሕርና ስለ ወንዞችም መምላት ጸልዩ። እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስ በረከቱን ሰጥቶ እስከ ልካቸው እንዲመላቸው፤ ለምድርም ልምላሜውን ሰጥቶ ደስ እንዲያሰኛት ሥጋዊን ሁሉ በረድኤት እንዲያጸና ለእንስሳትም ሁሉ ድኅነትን እንዲሰጥ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ አስቡን (አትርሱን) ስላሉን ሰዎች ጸልዩ። እግዚአብሔር በበጎ ያስባቸው ዘንድ በየጊዜውም ይቅር ይላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. *እግዚኦ ተሣሃለነ።*

ይካ. ይህችን ሳምንት ጌታ በበጎ ይፈጽማት ዘንድ ከኛም የጠላትን መፈታተን አርቆ ሰውነታችንን እንዲያድን ይቅር እንዲለን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይካ. ጌታችን አምላካችን ራርቶ ይቅር እንዲለን ልመናችንንም ተቀብሎ ለዚያ ለፋሲካው እንዲያበቃን የትንሣኤውንም ብርሃን በፍጹም ደስታ እንዲያሳየን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ።